**78**

# Midroc Newsletter

A BI-MONTHLY PUBLICATION OF THE OFFICE OF THE CHIEF EXECUTIVE OFFICER

This Newsletter provides customers, employees, suppliers, shareholders and the community at large with current information on major performance and other activities of the companies under the leadership of the CEO

**Volume 14, Issue No. 78** **July — August 2014**

MIDROC is a representative body of men and women with a common interest: "quality products and sustained services to every consumer and user". Together, we can make great strides, helping one another along the way in our respective



efforts and lending a base of support to our fellow citizens. If we have learned any lesson from the past years, here it is, indeed, that when people come together with the goal of working together, with a vision of development and change.

## ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አስመረቀ
## جامعة يونتي تخرج طلابا بتخصصات مختلفة



የተማሪዎች ምረቃ በተካሄደበት ዕለት
ዶ/ር አረጋ ይርዳው የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት፣ ዶ/ር ቡቴ የቢዝነስ ዴቬሎፕመንት ም/ፕሬዚዳንት እና ዶ/ር ብርሃኑ ሲሳይ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት

ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች በሁለተኛ፣ በመጀመሪያ ዲግሪና በዲፕሎማ ያሠለጠናቸውን 1,040 ተማሪዎች በአዲስ አበባና በአዳማ

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

خرجت جامعة يونتي طلابا تلقوا تدريبات في المجالات المختلفة على مستوى الماجستير والجامعة والدبلوم الذين يصل عددهم **1.040** طالبا في كل من مدينة

الى صفحة 2

በውስጥ ገጾቻችን

▶ ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ለሚያሠራው ትምህርት ቤት ............6
▶ የቴክኖሎጂ ግሩፕ የገ/ቁ/ብ/ የሕብረት ሥራ ማኅበር............6
▶ የሠራተኞች የህክምና ወጪ, ሽፋን ከፍ እንዲል ተደረገ............6

Inside Pages

▶ ከሠራተኞች ማኅደር............6
▶ ጠቅላላ ዕውቀት............7
▶ መልዕክት፣ ከቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር............8

## የአዳማ ካምፓስ የምረቃ ሥነ ሥርዓት በከፊል










## የደሴ ካምፓስ የምረቃ ሥነ ሥርዓት በከፊል







ጠቅላላ ዕውቀት

# ኢቦላ

ኢቦላ ቫይረስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው እ.ኤ.አ በ1976 ዓ.ም. ነው ናዛር ሱዳንና ያምቡኩ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ውስጥ ነው። ቦታዎቹ የገጠር መንደሮች፣ እርጥበትና ሙቀት በማይለየው ደን አካባቢ የሚገኙ ናቸዉ። የዓለም የጤና ድርጅት እንዳስታወቀው በዚያን ወቅት ሱዳን ውስጥ 284 ሰዎች በቫይረሱ ተይዘው 151 ህይወታቸውን አጥተዋል። በዴሞክራቲክ ኮንጎ ደግሞ 318 ታመው 280 ሞተዋል። ሱዳን ውስጥ እ.ኤ.አ በ1979 እንዲሁም 2004 ዓ.ም. በሽታው ዳግም ተከስቷል። ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ውስጥ ግን እያሰለሰ ለ10 ጊዜያት መደጋገሙን የዓለም የጤና ድርጅት የመዘገበው መረጃ ያመለክታል። ቫይረሱ ስሙን ያገኘዉ ኮንጎ ውስጥ በሽታው በተከሰተበት ሰሜናዊ የሀገሪቱ አካባቢ ከሚገኘዉ ኢቦላ ወንዝ ነው። ኤቦላ ወንዝ የታላቁ ኮንጎ ወንዝ ገባር የሆነው ሞንጋላ ወንዝ መገኛ ምንጭ መሆኑ ይነገርለታል። ቫይረሱ መነሻው ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን ህይወት በመቅጠፍ ይታወቃል። የዓለም የጤና ድርጅት እንደሚገልፀው በኢቦላ ቫይረስ ከተያዙ ሰዎች 90 በመቶው አይተርፉም። በቫይረሱ በፍጥነት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው። የበሽታው ምልክቶች ኃይለኛ ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ ህመም፣ ድንገተኛና ኃይለኛ ትኩሳት፣ ድካም፣ የቆዳ ሽፍታ፣ የዓይን መቅላት፣ የጉሮሮ ህመም፣ ማስመለስና ማስቀመጥ የበሽታው ምልክቶች ናቸው። በሽታው የኩላሊትና ጉበትን ተግባር በማስናከል አንዳንዴ አካል ውስጥም ሆነ ከውጭ የደም ፍሰት ያመጣል። ቫይረሱ ከአንዱ ወደሌላ ሰው በፍጥነት የሚተላለፍ በመሆኑም ይታወቃል።

የህክምና ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት አንድ ሰው በኢቦላ በተያዘ ከሁለት እስከ 21ቀናት ቫይረሱ በዚያ ሰው ውስጥ አቅሙን አጠናክሮ ማጥቃቱን ይጀምራል። በሰውነታችን ክፍት ቦታዎች ማለትም አይን፣ አፍንጫ፣ ድድ፣ ጆሮ፣ ፊንጢጣና በብልት በኩል የመድማት ምልክት ሊታይም ላይታይም ይችላል። በበሽታው የተጠቃው ሰው የምግብ ፍላጎቱ ይጠፋል፤ በሂደቱም አንጀትን እንዲሁም የመተንፈሻ አካላትን ማወክና መጉዳቱን ቀጥሎ ለህልፈት ይዳርጋል።

## የበሽታው መተላለፊያ መንገዶች

- በኢቦላ ከታመመ ሰው ቁስል፣ ደም፣ ምራቅ፣ ትውከት፣ አይነምድርና ሽንት ጋር በቀጥታ በመነካካት ወይም እነዚህ ፈሳሾች ወደ ጤነኛ ሰው ዓይን ከተረጨና ከገቡ፤
- ንጽህናቸው ባልተረጋገጠ ወይም ሌሎች ህሙማን የተጠቀሙበትን መርፌ ሳይቀቅሉ በመጠቀም፤
- የኢቦላ በሽታ ታማሚ የተጠቀመባቸውን ስለታማ መሳሪያዎች በመጠቀም፤
- በኢቦላ በሽታ የሞተ ሰውን አስከሬን በቀጥታ በመነካካት፤
- በኢቦላ በሽታ የሞተውን እንስሳ ሥጋ በመመገብ ናቸው።

እንደጤና ባለሙያዎች እምነትም ሰው ብቻ ሳይሆን እንስሳትም ቫይረሱ ለማሸጋገር ዓይነተኛ ሚና ይጫወታሉ። በተለይ የሌሊት ወፍ ከበሽታው አሸጋጋሪዎች ግንባር ቀደም ሳትሆን እንደማትቀር ትጠረጠራለች።

## በኢቦላ በሽታ መያዙ የተጠረጠረ ወይም የተያዘ ሰው ከገጠመን ምን ማድረግ አለብን?

- ታማሚውን በምንረዳበት ጊዜ ሰውነታችንን ከበሽታው መከላከል የሚያስችለንን የእጅ ጓንት፣ የአይን መከላከያ መሣሪያ (ጎግል) እና የአፍንጫና የአፍ መሸፈኛ ማስክ መጠቀም፤



- የታመመውን ሰው ወድያውኑ ለአስፈላጊ ህክምናና እርዳታ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ጤና ተቋም መውሰድ፤
- በኢቦላ በሽታ የተጠረጠረ ሰው በሚገኝበት ወቅት ወድያውኑ በአቅራቢያው ወደሚገኘው ጤና ተቋም ወይም ጤና ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረግ፤
- በበሽታው መያዙ የተጠረጠረ ወይም የታመመ ሰው የተጠቀመባቸውን አልባሳትና መኝታውን በበረኪና ማጠብ ይኖርብናል።

## ለኢቦላ በሽታ ተጋላጭ የሆኑት ማናቸው?

- በሽታው ከታመመ ሰው የሚወጣውን ደምና ሌሎች የሰውነት ፈሳሾች በቀጥታ በመነካካት የሚተላለፍ በመሆኑ ከታመመው ሰው ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው በበሽታው ሊያዝ ይችላል።
- በሽተኛውን በሚመገቡበትና በሚንከባከቡበት ወቅት የእጅ ጓንትና ሌሎች መከላከያ መሣሪያዎች ሳያደርጉ ከሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪ የሚፈፅሙ ሰዎች በቀላሉ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ።
- በኢቦላ በሽታ የሞተውን ሰው አስከሬን ያለ እጅ ጓንትና ሌሎች የመከላከያ መሣሪያዎች የምንነካካ ከሆነ በቀላሉ በበሽታ ልንጠቃ እንችላለን።

## የኢቦላ በሽታን እንዴት ልንከላከል እንችላለን?

- የእጅ ጓንት፣ የዓይን ጎግል እና ሌሎች የሰውነት መከላከያ መሣሪያዎችን በመጠቀም በበሽታው ከተጠቃ ሰው ውስጥ ከሚወጣው ማንኛውም ፈሳሽ ጋር በቀጥታ ባለመነካካት፤
- ያለ እጅ ጓንት በበሽታው የተጠቃውን ሰው ቁስል አለመንካት፤
- በኢቦላ በሽታ የተያዘው ሰው የተጠቀመውን መርፌና ሌሎች ስለት ያላቸውን መሣሪያዎች አለመጠቀም፤
- በኢቦላ በሽታ መያዙ የተጠረጠረና የሞተ እንስሳን ሥጋ አለመመገብ፤
- በኢቦላ በሽታ የሞተን ሰው አስከሬን ያለጓንትና ሌሎች የመከላከያ መሣሪያዎች ያለመንካት፣ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈፀም ማድረግ ፤ እንዲሁም ከቀብር በኋላ ያለውን ሥነ-ሥርዓት ማሳጠር፤
- የታመመውን ሰው ከረዳን ወይም በበሽታዉ ምክንያት የሞተውን ሰው አስከሬን ከነካን በኋላ እጃችንን በውሃና በሳሙና በደንብ መታጠብ፤

## በቤት ውስጥ መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ

- በኢቦላ በሽታ የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰውን በተቻለ መጠን ለብቻው በተዘጋጀ ቦታ መለየት፣
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረን ሰው ወደ ጤና ተቋማት በምንወስድበት ወቅት ከታማሚው ጋር አላስፈላጊ ንክኪ አለማድረግ፤
- በበሽታው ከተጠቃ ወይም ከተጠረጠረ ሰው ወይም የሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪ ከተፈጠረ ወዲያውኑ እጃችንን በውሃና በሳሙና መታጠብ፤
- በኢቦላ በሽታ የተጠቃውን ሰው በምንረዳበት ወይም በምንንከባከብበት ወቅት የእጅ ጓንት፤ የዓይን ጎግል፤ የፊት መሸፈኛ እና ሌሎች የሰውነት መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም፤
- በበሽታው የተጠቃ ወይም የተጠረጠረ ሰው የሰውነት ፈሳሽ መሬት ከበከለ በረኪና ይጨምሩበት፤ ከ15 ደቂቃ በኋላም ይፀዳ፤ በቆሻሻ የተነካኩ ቁሳቁሶችና አልባሳት መቃጠል ይኖርባቸዋል፤
- በኢቦላ በሽታ ታሞ የሞተ ሰው የቀብር ሥነ-ሥርዓት ሲፈፀም ከአስከሬን ጋር ንክኪ አለማድረግ፤ የጋራ እጅ መታጠቢያም አለመጠቀም፤
- የቀብር ሥነ-ሥርዓት ሲፈፀም አስከሬኑን በፕላስቲክ ከረጢት መጠቅለል፣ በሰለጠነ የጤና ባለሙያ ምክር መታገዝ ያስፈልጋል።



ምንጭ፡- ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለህብረተሰብ ጥንቃቄ ካሰፈረው ጽሑፍ የተወሰደ

# መልዕክት፣ ከቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር

## መልካም የሥራ ዘመን!

በአገራችን ታሪክ ውስጥ በአዲስ መልክ በተጀመረውና ከምንግዜውም ይልቅ ጥራቱን እያስጠበቀ በሚገኘው በግሉ የትምህርት ዘርፍ ፈርቀዳጅ በመሆን በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ብቁ ዜጎችን በማፍራት ሂደት ላይ የሚገኘው ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ያስለጠናቸውን ተማሪዎች ሲያስመርቅ ደስታ ይሰማዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን እያስለጠነ የሚያስመርቃቸውን ተማሪዎች ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱና በተለይም አገሪቱ በምትፈልጋቸው የትምህርት መስኮች ታላላቅ ምሁራንን ለማፍራት በመቻላችን ለልማት ዘርፉ አስተዋፅኦ በማድረጋችን ኩራት ይሰማናል፡፡

በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ከምትገኝበት ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ለመላቀቅና ድህነትን ለማስወገድ ለምታደርገው ጥረት የተማረ የሰው ኃይል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የጐላ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የሠለጠኑ ሙያተኞችን በየዘርፉ በጥራት ለማግኘት እንዲቻል መንግሥት የቀየሰው የትምህርት ፖሊሲ በመንግሥት ተቋማት ብቻ ሊከናወን የሚችል ባለመሆኑ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለዚህ በጐ ተግባር መሳካት ከፍተኛ ገንዘባቸውን በማፍሰስ መሳተፋቸው ለጋራ ዕድገት ወሳኝ ሆኖ ለማየት ችለናል፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ደረጃዎች የተማሩ ዜጐችን በብቃት ለማፍራት የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ የቆየው በቂ ዕውቀትን በመስጠት ኃላፊነት በተጣለባቸው ምሁራንና የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ጭምር በመሆኑ እስከዛሬ ከዩኒቨርሲቲው የተመረቁ ምሁራን የሚያስመዘግቡት ውጤት አመላካች ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን የሚሠጣቸው ልዩ ልዩ የትምህርት ዘርፎች ለአገራችን ዕድገት ወሳኝ በመሆናቸው ዕውቀቱን ቀስመው ለሥራ የሚሠማሩት ምሁራን የሥራ ውጤት በተግባር እያስመሰከረ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን በአገራችን የትምህርትና የአገልግሎት ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ታላላቅ ምሁራንን በልዩ ልዩ መመዘኛዎች በማየት ዕውቅና በመስጠት በአገልግሎታቸው በክብር የሚወደሱበትን ልዩ ፕሮግራም በማስተዋወቁና በየዓመቱ ሽልማት መስጠቱ በአርአያነት የሚያስጠራው ተግባር እየሆነ ይገኛል፡፡ ይህንኑ ታላቅ ተግባርም አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡

በዚህ ዓመት ዩኒቨርሲቲያችን በአዲስ አበባ፣ በአዳማና ለመጀመሪያ ጊዜ ደግሞ በደሴ ካምፓስ ያስለጠናቸውን ተማሪዎች ሲያስመርቅ ምሩቃንንም ሆነ ሲደግፏቸው የነበሩ ቤተሰቦቻቸውን እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት መጪው ዘመን ምሩቃን በሥራ ተሰማርተው ያገኙትን ዕውቀት በተግባር የሚተረጉሙበት እንዲሆን በመመኘት ነው፡፡ በተጨማሪም አዲሱ ዓመት ለቴክኖሎጂ ግሩፑ ኩባንያዎች ሠራተኞች መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆን እመኛለሁ!



ዶ/ር አረጋ ይርዳው
Dr. Arega Yirdaw
ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር፣ ሚድሮክ ኢትዮጵያ
Chief Executive Officer, MIDROC Ethiopia

*Address: Office of the Chief Executive Officer, MIDROC Ethiopia*
*Fax: +251-11-371-5988 / 372-4977*
*P.O. Box: 5787, Addis Ababa Ethiopia*
*E-mail: ceomidroc@ethionet.et*
*Website: www.midroc-ethiotechgroup.com*

በነፃ የሚታደል (Distributed at no Cost)